# የበዳይ ተበቃይ

ምስኪን ማርቲን ቦርማን
ፖልፖትና ሜንጌል ኤድዋርድ ሮችማን
ጎብልስ አረመኔ የፖግሮም ፈጣሪ
ሚሎሴቪችና ፒኖሼ ካራዲች
ሌሎቹም ሌሎቹም ሰብአዊ አውሬዎች

ቱትሲ ገዳዮቹ ካምባንዳ ኣካይሱ
ኢንቴራሀምዌ ና ቀይ ሽብር ሆሎኮስት
ጉሎ ካኪ ለባሽ ባለቡና ሸሚዝ ባለረዥም ካራ

ፈጥሯችሁ በነበር በዚች በኛ ምድር
በዚህ በኛ ዘመን ሥልጡን ፖለቲካ
ህሊና ደንብሾ ባንዳ አንጃነቱ ክህደት በኮራበት
ገዳይ ዐይን አውጥቶ በሰለባው ሲዝት

ይሻላችሁ ነበር እዚህ ከኛ ጋራ
ከመሳደድ ኑሮ
ሁሌ ተሰውሮ ሁሌ እንደሰስ ባኖ
ከፍርድ ለማምለጥ
ከናዚ አዳኞች ከሀጋና በቀል
ፀረ- ናዚ *ሳብራ ከላቲኖው ፋኖ

እንደ ኢሠፓ ሀይሉ የጎብልስ መንትያ
ታሪክ አውገርጋሪ
ትኖሩ ነበረ በሰላም በክብር
ፈጥሯችሁ በነበር በዚች በኛዋ ሀገር

የዕንቁ ደበበን ደም የሲሳይ ተቀባን
የአሚና መሀመድ ደረጄ አለሙን
ተሻለ ተስፋዬ ነጂብና ከንፈን

አየለ መንግሥቱ የትግል ሐረጌ አዛለች ፀጋዬን
ጣቱ እስኪዶለዱም ጠቁሞ ጠቁሞ
እጁ መጅ አውጥቶ ክንዱ እስኪዝል ገርፎ
ተክለሀይማኖት ኮልፌ ፒያሳ መርካቶ
ያዕላፍ ታጋይን ደም ያንቆረቆረው
አንጃ ነው ኢሰፓ ዘንድሮ ወያኔ ብርሀኑ ደቡር
ግራንድ ኢንኩዊዚተር

ትኖሩ ነበረ በተቃዋሚነት በመንግሥት  ሹምነት በሰላም በክብር
ጌስታፖ ናዚዎች ፈጥሯችሁ በነበር በዚች በጉድ አገር

ግና አልታደላችሁ
ህግ የሌለው ሽፍታ ወያኔ የላችሁ
እንደዚህ እንደኛ የወንጀል ጉሮኖ የገዳይ  አለኝታ
ወንጀል መሸፈኛ የ "ተቃዋሚነትን " ወግ የሚቸራችሁ
ለትግል ማኮላሻ ታሪክ መበረዣ ታጋይ ማሳደጃ አገልግሎታችሁ

ትኖሩ ነበረ በነፃነት አየር በወያኔ ጥላ
እያሸበራችሁ እያሳደዳችሁ
ታሪኩን ጥላሸት ገድሉን ረግማችሁ
ከትላንቱ ሽብር ከ*ዳኻው ከርቸሌ
ከደርጉ ጽህፈት ቤት ከፒንሳ ጉጠቱ
ከቀይ ሽብር ቶርቸር ከነፃው ርምጃ ከነሲብ ፍጅቱ
ከከነማ *ኦሽዊትዝ ከህዝብ "ደህንነት"
ሾልኮ ተሰውሮ ያመለጠን ሁላ በድቅድቁ  ለሊት
መሠረተ ለዋጭ  ኢህአወሊ  ኢህአፓ የግፈኞች ውጋት
ያውሎ ነፋስ ቀንዲል  ሊኖር ህያው ሆኖ የማለ ላይጠፋ
የትላንትም ሆነ የዛሬ ሰለባ
መቼም አትተዉት  አፈር እስካልገባ

ሀይሉ አርአያ የኛው *እርነስት ዙንደል የክህደት ሽበቱ
ወንጀል ከለማበት ያገረሸበቱ
አዲስ ታሪክ ፅፎ ቀይ ሽብር መች ነበር?

ዲሞን በዲሞትፈር ሽብር እኮ አይደለም
ከነበረም እሱ ሽብር አይባልም
ባብዮት ጎዳና የሚኖር ምንጊዜም
የህዝብ ጥያቄ ቀይ ሽብር ይፋፋም
የስታሊን ፍጡር ነው በኛ አልተጀመረም

አሁንም ይወገድ ምሱ ነው ቀይ ሽብር
እሰይ ደስ ማለቱን አሁንም እንዘምር
እምቢ አሻፈረኝ አልገዛም ለሚል
ይወገድ ቀሪውም ሌሎችን ሳይበክል

ታሪክ ግን አትሞትም
ሁሌም አለሁኝ ባይ ኗሪ ለዘላለም
ባምባ ገነን 'ግረ ሙቅ ቢሰልልም ድምፁዋ
'እውነቶች' ተፅፈው ቢማልም በስሟ
ማሳደድዋን አትተው ፍትህን መሻትዋ
ሀገር ቀን ወጥቶላት ባራት እግሯ ስትቆም
በፍርድ ወንበሯ ላይ ፍትህን ስታስችል
ተራሮች ሲሸሹ ጠፍቶ መሰወሪያ

ያኔ አንተን አያርገኝ የከደት አርአያ
የበዳይ ተበቃይ የተገላቢጦሽ ህሊና አልቦ እሪያ
አንተንም አያርገኝ ደቡር አሳማውን
እንዲሁም ያን ሼባ ባለበዙ ቀለም
ከጥንት እስከዛሬ ወርዶ ያላበቃው የጥላቻው መስፍን
የሙብት ጠበቃ የፍትህም ቁንጮ ምሳሌ ነኝ ባዩን
ለሙብት ነፃነት ዱር ቤቴ ያሉትን አላውቅም ያለውን

ትውልድ ረጋሚ የነበዘ ምሁር የነቃ ብርሌ መሳይ አስመሳዩን
የትላንት ማርክሲስት የትላንት ኢሠፓ ዛሬ ሪፓብሊካን
ለቆሸሸ ሥራው ወንጀል ለመሸፈን ታሪክ አድበስባሹን

ያምባገነን ሎሌ የግፍ ዘመን ሹምባሽ የከፉ ቀን ጅቦች

ወላድ ልጇ ታርዶ ደምምባ ስታዘንብ
በፋሺስቶች ድግስ ሀይሎጋ ዕልል ባዮች
ለትላንት ፋሺስት ለዘንድሮው ሁቱ ያሸረገዱቱ
ነፍሳቸው ቆሸሻ ታሪኳም ከርፍቶ ህሊና ደንብሾ
“ሰው” እንዴት ይቆማል ሰዎች መሀል ገብቶ???

*ሳብራ፣ የአይሁድ አርበኛ
*ዳኻው፣ የናዚ የፍጅት ካምፕ
*አሽዊትዝ፣ የናዚ የፍጅት ማዕከል
*እርነስት ዙንደል፣ የሆሎኮስትን ፍጅት የካደ ኔዎ ናዚ ባሁኑ ወቅት በዚሁ ወንጀል ተፈርዶበት ጀርመን ውስጥ የእስር ዘመኑን ጨርሶ በቅርቡ የተፈታ